በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
Federal Democratic Republic of Ethiopia
The Federal Ethics and Anti-Corruption Commission

የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት
Ethiopian Biodiversity Institute
የደረሰበት ቀን 23/7/2013
የመዝገብ ቁጥር 2865
የደብ ቁጥር ኢብሕ-248
Received on

ቀን / Date 24/07/2013
ቁጥር / Ref.No. 20/002450/ፍዝ/5987

ለኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት

<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፣ <u>የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎችን አሰራርና አደረጃጀት ለመወሰን የወጣዉን መመሪያ ስለማሳወቅ</u>

የፌዴራል የስነምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅን ለመሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 1236/2013 መሰረት በመንግስት መስሪያ ቤቶች እና በመንግስት የልማት ድርጅቶች ውስጥ የሚደራጁት የስነምግባር መከታተያ ክፍሎች ተጠሪነት በቀጥታ ለኮሚሽኑ መሆኑ ይታወቃል፡፡ እነዚህ የስነምግባር መከታተያ ክፍሎች ስራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት በግልፅነት፣ በተጠያቂነትና በገለልተኝነት መርህ ላይ ተመስርተዉ በአግባቡ ለመፈፀም እንዲችሉ፣ ከተቋማቸው እና ከኮሚሽኑ ጋር የሚኖራቸውን የስራ ግንኙነት ለመምራት የሚስችል ዝርዝርና ግልጽ አሰራር መዘርጋት አስፈላጊ መሆኑ ይታመናል፡፡

በዚህም መሠርት ኮሚሽኑ በአዋጅ ቁጥር 1236/2013 አንቀፅ 23 ንዑስ አንቀፅ 2 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን ‹‹የሥነ ምግባር መከታተያ ክፍሎችን አሰራርና አደረጃጀት ለመወሰን የወጣዉን መመሪያ ቁጥር 20/2013›› በተቋሙ ተግባራዊ እንዲደረግ እናስታውቀለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ሀ.ጋ አራጌ ትኩዬ
ኮሚሽነር

<u>እንዲያዉቁት፣</u>

- ለም/ኮሚሽነር ጽቤት

<u>ግልባጭ፣</u>

- ለሥነምግባር መከታተያና ሙስና መከላከል ዳይሬክቶሬት
  <u>ፌ.ሥ.ፀ.ሙ.ኮ</u>

# የፌዴራል የስነምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን

# የስነምግባር መከታተያ ክፍሎችን አሰራርና አደረጃጀት ለመወሰን የወጣ መመሪያ

## መመሪያ ቁጥር 20/2013

The Federal Ethics and Anti-Corruption Commission

መጋቢት/2013

አዲስ አበባ

# የስነምግባር መከታተያ ክፍሎችን አሰራርና አደረጃጀት ለመወሰን የወጣ መመሪያ

## መመሪያ ቁጥር 20/2013

ሙስና እና ብልሹ አሰራርን በመንግስት መስሪያ ቤቶች እና በመንግስት የልማት ድርጅቶች ውስጥ ተቋማዊ በሆነ መንገድ መከላከል አስፈላጊ በመሆኑ፣

የትውልድ ስነምግባር ግንባታ ስርዓት በአለው መንገድ በማካሄድ ሙስና እና ብልሹ አሰራርን የሚፀየፍ እና በተደራጀ መንገድ የሚታገል ህብረተሰብ መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ፣

የተሻሻለውን የፌደራል የስነምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል በወጣው አዋጅ መሰረት የስነምግባር መከታተያ ክፍሎች ተጠሪነት በቀጥታ ለኮሚሽኑ በመሆኑ ከዚህ አኳያ በመንግስት መስሪያ ቤቶች እና በመንግስት የልማት ድርጅቶች ውስጥ የሚደራጁት የስነምግባር መከታተያ ክፍሎች አሰራር በዝርዝር መደንገግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የስነምግባር መከታተያ ክፍሎች ስራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት በግልፅነት፣ በተጠያቂነትና በገለተኝነት መርህ መሰረት ለመፈፀም እንዲችሉ፣ ከተቋማቸው እና ከኮሚሽኑ ጋር የሚኖራቸውን የስራ የግንኙነት ስርዓት ግልጽ በማድረግ መዋቅራዊ አደረጃጀት፣ የስራ ደረጃ፣ ምደባ፣ ቅጥር፣ ዝውውር፣ ስንበት፣ የዓመት ፈቃድ፣ የዲስፒሊን እርምጃ አወሳሰድ ስነስርዓት እና የስራ አፈፃፀም ምዘና እንዴት እንደሚከናወን በዝርዝር መደንገግ አሰፈላጊ በመሆኑ፣

የፌዴራል የስነምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ለመሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 1236/2013 አንቀፅ 23 ንዑስ አንቀፅ 2 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

The Federal Ethics and Anti-Co... Commission

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የስነምግባር መከታተያ ክፍሎችን አሰራርና አደረጃጀት ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 20/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉሜ የማያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. **"አዋጅ"** ማለት የተሻሻለው የፌደራል የስነምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ እንደገና ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 1236/2013 ነው፣
2. **"ኮሚሽን"** ማለት በአዋጅ ቁጥር 1236/2013 መሰረት የተቋቋመው የፌደራል የስነምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ነው፣
3. **"ኮሚሽነር"** ማለት እንደቅደም ተከተሉ የፌደራል የስነምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ወይም ምክትል ኮሚሽነር ነው።
4. **"የመንግስት መስሪያ ቤት"** ማለት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በመንግስት በጀት የሚተዳደር እና የፌዴራል መንግስቱ ስራዎች የሚከናወኑበት ማናቸውም መስሪያ ቤት ነው፣
5. **"የመንግስት የልማት ድርጅት"** ማለት የመንግስት ባለቤትነት ድርሻ በሙሉ ወይም በከፊል ያለበት ማንኛውም የፌዴራል መንግስት የልማት ድርጅት ወይም የአክሲዮን ኩባንያ ነው፣
6. **"ተቋም"** ማለት የስነምግባር መከታተያ ክፍሉ የሚሰራበት የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም የመንግስት ልማት ድርጅት ነው፣
7. **"የተቋሙ የበላይ ኃላፊ"** ማለት የስነምግባር መከታተያ ክፍሉ የሚሰሩበት የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም የመንግስት ልማት ድርጅትን የሚመራ ዋና የስራ ኃላፊ ነው፣

The Federal Ethics and Anti-Corruption Commission

8. **"የስነምግባር መከታተያ ክፍሎች"** ማለት በመንግስት መስሪያ ቤት ወይም በመንግስት የልማት ድርጅት ውስጥ የስነምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ስራውን በየተቋማቱ ለማስራት የሚያደራጃቸው አደረጃጀቶች ናቸው፣
9. **"በዓላማ ፈጻሚ ትይዩ የስራ ደረጃ"** ማለት የስነምግባር መከታተያ ክፍሎች የሚኖራቸው የስራ ደረጃ በተደራጁባቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶች ወይም የመንግስት የልማት ድርጅቶች ውስጥ የተቋሙን ዓላማ ለማሳካት በተዳራጁት ዓላማ ፈፃሚ የስራ ክፍሎች /core process/ በከፍተኛው የተሰጣቸውን የስራ ደረጃ በእኩል ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ይሆናል ማለት ነው፣
10. **"ዓላማ ፈፃሚ"** ማለት የስነምግባር መከታተያ ክፍሎች በተደራጁባቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶች ወይም የመንግስት የልማት ድርጅቶች ውስጥ የተቋሙን ዓላማ ለማሳካት የተዳራጁትን ዋና ዓላማ ፈፃሚ የስራ ሂደት /core process/ ማለት ነው፣
11. **"የአሰራር ግንኙነት"** ማለት በየተቋሙ የሚደራጁት የስነምግባር መከታተያ ክፍሎች ከሚሰሩበት ተቋም እና ከኮሚሽኑ ጋር የሚኖራቸው የስራ ግንኙነት ነው፣
12. **"የስራ ቦታ"** ማለት የስነምግባር መከታተያ ክፍሉ የተደራጀበት የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም የመንግስት የልማት ድርጅት ዋና መስሪያ ቤት የሚገኝበት ቦታ ነው፣
13. **"ልዩ ልዩ አገልግሎት"** ማለት የስነምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊና የክፍሉ ሠራተኞች እንዲሰጣቸው የሚጠይቁት የጡረታ፣የፈቃድ፣ የስራ ልምድ፣ዋስትና፣የትብብር ደብዳቤ እን መሰል አገልግሎቶች ናቸው፣
14. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

## 3. የስነምግባር መከታተያ ክፍል ዓላማዎች

1. በሚያስተባብሯቸው የመንግስት መ/ቤቶች ወይም የልማት ድርጅቶች የስራ ኃላፊዎችን እና የሠራተኞችን የስነምግባርና የሞራል እሴቶችን መገንባት፣
2. የሙስና ወንጀልን እና ብልሹ አሰራርን መከላከል፣
3. በተቋሙ ውስጥ የሚገኙ የህዝብ ተመራጮች፣ የመንግስት ተሿሚዎች፣ የመንግስት ሰራተኞች እና የመንግስት ልማት ድርጅቶች የስራ ኃላፊዎች እና ሰራተኞች ሃብት እንዲያሳውቁ፣ እንዲያስመዘግቡ እና እንዲያሳድሱ በማድረግ የግልፅነት እና የተጠያቂነትን ስርዓት ለመፍጠር፣

4. ለፀረ ሙስና ትግል አጋዥ የሚሆን የሠራተኛ ንቅናቄ በመፍጠር ሠራተኛው የፀረ ሙስና ትግል ባለቤት እንዲሆን ማስቻል፣
5. በስነምግባር ግንባታና በሙስና መከላከል ጉዳዮች ተቋሙን ማማከር እና ለፀረ ሙስና ትግሉ ሚና ያላቸውን ባለድርሻ አካላት ማስተባበር ነው።

4. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በፌደራል ደረጃ በየደረጃው በሚገኙ የመንግስት መስሪያ ቤቶች እና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

## ክፍል ሁለት

## የስነምግባር መከታተያ ክፍል ተጠሪነት፣ ተግባርና ኃላፊነት እና አደረጃጀት

5. ተጠሪነት

1. ስነምግባር መከታተያ ክፍል ተጠሪነቱ ለፌደራል ስነምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ይሆናል፣
2. የቅርንጫፍ የስነምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊ ተጠሪነቱ ለዋናው መ/ቤት የስነምግባር መከታተያ ክፍል ዳይሬክቶሬት ነው።

6. የስነምግባር መከታተያ ክፍል ተግባርና ኃላፊነት

1. የተቋሙ አመራርና ሰራተኞች በስነምግባርና በሙስና መከላከል ያላቸውን ክፍተት በጥናት ይለያል፣ የስልጠና ሰነድ ያዘጋጃል፣ ተግባር ተኮር ስልጠና ይሰጣል፣
2. በመልካም ስነምግባር ግንባታ፣በሙስና መከላከል ስትራቴጂዎች በተለያዩ ስነምግባርና የፀረ መስና ጉዳዮች ላይ ለሠራተኞች እና አመራሮች ስልጠና ይሰጣል፣
3. ለሙስናና ብልሹ አሰራር የተጋለጡ እና ሊጋለጡ የሚችሉ የአሰራር ስርዓቶችን ማጥናት ወይም እንዲጠኑ ማድረግ፣ የተሰጡ የመፍትሄ ሃሳቦችን ማቅረብ፣ ተግባራዊ መሆናቸውን መከታተል፣ በማይፈፅሙት ላይ ተገቢ የሆነ እርምጃ እንዲወሰድ ለኮሚሽኑ ማሳወቅ፣
4. በተቋሙ ውስጥ የሚገኙ የህዝብ ተመራጮች፣ የመንግስት ተሿሚዎች፣ የመንግስት ሰራተኞች፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የስራ ኃላፊዎች እና ሰራተኞች ከተሰጣቸው ኃላፊነት፣ ከመቆጣጠር እና ከመወሰን ስልጣን ጋር በተያያዘ የሚፈጠር



The Federal Ethics and Anti-Corruption Commission

የጥቅም ግጭትን በጥናት ይለያል፣ የመከላከያ ዘዴዎችን ያመነጫል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣

5. በተቋሙ ውሰጥ ሙስና ለመፈፀም የሚያስችል ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ሲገምት ወይም ሲጠረጠር እና ጥቆማ ሲደርሰው ድርጊቱ ከመፈፀሙ በፊት ኮሚሽኑን እና የተቋሙን የበላይ ኃላፊ በማሳወቅ አስቸኳይ የሙስና መከላከል ስራ ይሰራል፣ ሂደቱ እንዲቋረጥ ወይም አስፈላጊውን ማስተካከያ እንዲደረግ ያደርጋል፡፡ ሆኖም ግን በተደረገው የአስቸኳይ የሙስና መከላከል ተግባር ሙስና ስለመፈፀሙ ጥርጣሬ ሲኖረው በህግ የመመርመር እና የመክሰስ ስልጣን ላለው አካል ያሳውቃል፣
6. በተሻሻለው የኮሚሽኑ የሃብት ማሳወቅ እና ምዝገባ መመሪያ መሰረት የተቋሙ ሁሉም አመራሮችናን ሠራተኞች መረጃዎቹን ያደራጃል፣ ወቅታዊ ያደርጋል፣ ሀብታቸውን እንዲያሳውቁ፣ እንዲያስመዘግቡ፣ እንዲያሳድሱ ያደርጋል፣ የምዝገባ ሰነዱንም ለኮሚሽኑ ይልካል፡፡ ከኮሚሽኑ ፀድቆ የተላከትን የሃብት ምዝገባ ሰርትፊኬት ለአስመዝጋቢው ይሰጣል፣
7. በተቋሙ አዲስ የተሾሙ፣ የተቀጠሩ አመራሮችና ሠራተኞች ስራ ከመጀመራቸው ወይም የቅጥር ፎርም ከመሙላታቸው በፊት ሃብታቸውን እንዲያስዘግቡ ያደርጋል፣
8. በተቋሙ ውስጥ ያሉ ሀብት አስመዝጋቢዎች አገልግሎት ሲያቋርጡ ከስራ ክፍሉ ክሊራንስ እንዲወስዱ ያደርጋል፡፡ በተቋሙ አገልግሎት ለሚያቋርጡ የሀብት አስመዝጋቢዎች በህጉ መሰረት ዳግም ምዝገባ እንያከናውኑ በማድረግ ሰርተፊኬትና ክሊራንስ ይሰጣል፣ ይህንኑ ለኮሚሽኑ ያሳውቃል፣
9. የተቋማት ስነምግባር መመሪያ ያዘጋጃል፣ እንዲፀድቅ ያድርጋል፣ ተፈፃሚነቱን ይከታተላል፣
10. በመልካም ስነምግባርና ሙስና መከላከል ዙሪያ ግንዛቤ የሚፈጥሩ የተለያዩ የሚዲያ መልዕክቶች እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ያሳትማል፣ ያስተላልፋል፣
11. በኮሚሽኑና በተቋሙ የሚዘጋጁ የስነምግባር ግንባታና የሙስና መከላከል መልዕክቶችን መደበኛና ማህበራዊ ሚዲያዎችን በጠቀም ተደራሽ ያደርጋል፣
12. በስነምግባራቸው የተመሰገኑ እና ለሌሎች አርአያ የሆኑ ሠራተኞችንና አመራሮችን በመመሪያው መሰረት በመለየት የዕውቅና መድረክ ያመቻቻል፣እውቅናና ማበረታቻ ሽልማት እንዲገኙ ያደርጋል፣

13. ተቋሙ የትምህርት ተቋም ከሆነ የተማሪዎች የስነምግባር ክበብ ያደራጃል፣ ያጠናክራል፣ ስልጠና ይሰጣል፣ እንዲሰጥ ያደርጋል ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣
14. የስነምግባር ጉድለትና የሙስና መከላከል ጥቆማ አቅራቢዎች ሚስጥራዊነት ሊያረጋግጥ የሚችል ስርዓት ይዘረጋል፣ ስራ ላይ ያውላል፣ ጥቃት እንዳይደርስባቸው ከለላ እንዲሰጣቸው ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣
15. በተቋሙ የሰው ኃይል ቅጥር፣ ደረጃ ዕደገት፣ ዝውውር፣ ስልጠና ወይም አገልግሎት መረጃ ላይ ሊፈጸም የተሳቡ የሙስና ወንጀል ላይ ጥቆማዎችን ይቀበላል፣ድርጊቱ ከመፈፀሙ በፊት የሙስና መከላከል ስራዎችን ይሰራል፣
16. በተቋሙ ውስጥ የሚሾሙ ወይም የሚመደቡ ወይም የሚቀጠሩ የስራ ኃላፊዎች እና ሰራተኞች ስራ ከመጀመራቸው በፊት የስነምግባር እና የሙስና መከላከል ስልጠና ይሰጣል፣
17. የፀረ ሙስና ህጎች መከበራቸውን ይከታተላል፣ ስለአፈፃጸማቸው እና ስለሙስና መከላከል ለተቋሙ ምክር አገልግሎት ይሰጣል፣
18. በስነምግባር ግንባታ እና በሙስና መከላከል ድርሻ ከአላቸው አካላት ጋር የስራ ግንኙነት እንዲፈጠር ያስተባብራል፣
19. በተቋሙ ውስጥ አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የፀረ ሙስና ንቅናቄ እንዲፈጠር ያድርጋል፣
20. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

7. አደረጃጀት

1. ኮሚሽኑ በመንግስት መስሪያ ቤቶች ወይም በመንግስት ልማት ድርጅቶ ውስጥ የስራውን ስፋት፣ የሚንቀሳቀሰውን የሃብት መጠን እና የሰው ኃይል ግምት ውስጥ በማስገባት የሚያስፈልገውን አደረጃጀት እና የሰው ሀይል ብዛት ይወስናል፣
2. በተቋማት ውስጥ የሚደራጀው የስነምግባር መከታተያ ክፍል ዳይሬክትሬት ወይም ቡድን ወይም ባለሙያ በተደራጀበት የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም የመንግስት ልማት ድርጅት ውስጥ በአለው የዓላማ ፈፃሚ ከፍተኛው የዳይሬክቶሬት ወይም ቡድን ወይም ባለሙያ ደረጃ ይሆናል፣
3. በቅርንጫፍ ደረጃ የሚደራጀው የስነምግባር መከታተያ ክፍል ዳይሬክትሬት ወይም ቡድን ወይም ባለሙያ በተደራጀበት የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም የመንግስት ልማት ድርጅት

ቅርንጫፍ ውስጥ እንደየአግባብነቱ በአለው የዓላማ ፈፃሚ ከፍተኛው የዳይሬክቶሬት ወይም ቡድን ወይም ባለሙያ ደረጃ ይሆናል፣

4. በመንግስት መስሪያ ቤት ወይም በመንግስት ልማት ድርጅት ውስጥ የሚደራጀው የስነምግባር መከታተያ ክፍል ዳይሬክቶሬት፣ ቡድን እና የባለሙያ ስያሜ ኮሚሽኑ በሚሰየመው ስያሜ መሰረት ይሆናል።

## 8. ተቋማት ከስነምግባር መከታታያ ክፍሉ ጋር የሚኖራቸው የአሰራር ግንኙነት

1. የመከታተያ ክፍሉ እቅድ አቀዶ ሲልክ ምርምሮ ያፀድቃል፣
2. ለስራ ክፍሉ የሚሆነውን ማስፈፀሚያ ዓመታዊ በጀት ይመድባል፣
3. ወራሀዊ የስራ አፈፃፀም ርፖርት ይቀበላል፣
4. በስነምግባር ግንባታ እና በሙስና መከላከል ተግባር ላይ ያልተቋረጠ ድጋፍ እና ክትትል ያድርጋል፣
5. የስነምግባር መከታተያ ክፍሉ ሰራተኞች በተቀመጠው ኬሬር መሰረት ደመወዝ፣ ጥቅማጥቅም እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ አገልግሎቶችን ይሰጣል፣
6. ለስራው ተስማሚ የሆነ ቢሮ፣ ድጋፍ ሰጭ ሰራተኛ እና ለስራው አስፈላጊ የሆኑ የስራ መሳሪያዎች እንዲሟሉ ያደርጋል፣
7. የውስጥ እና የውጭ ኦዲተሮችን ሪፖርት ለመከታተያ ክፍሉ ያሳውቃል፣
8. እንደየአግባብነቱ የስነምግባር መከታተያ ክፍሉ ኃላፊ ወይም ቡድን ወይም ባለሙያ በማኔጅመንት ኮሚቴ ስብሳባ ያለድምፅ እንዲሳተፍ ያደርጋል። ሆኖም ግን በእቃ ግዥ፣ በሎጀስቲክስ አቅርቦት፣ በሰው ሀይል ቅጥር እና በመሳሰሉት ስራዎች በኮሚቴ አባልነት እንዳይሳተፉ ያደርጋል፣
9. የስነምግባር መከታተያ ክፍሉ የስራ ግንኙነቱ ከተቋሙ ኃላፊ ጋር ብቻ ይሆናል፣
10. የስነምግባር መከታተያ ክፍሉ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ለስራው የሚያስፈልገውን፣ የሚጠይቀውን መረጃና ሌሎች ድጋፎችን በመስጠት መተባበር ይኖርበታል።

## 9. የስነምግባር መከታተያ ክፍሎች ከሚሰሩበት ተቋም ጋር የሚኖራቸው የአሰራር ግንኙነት

ማንኛውም የመከታተያ ክፍል፡-

1. ከስነምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን የሚሰጣቸውን መነሻ እቅድ፣ ያሉትን ወቅታዊ ሁኔታዎች ለሚሰሩበት ተቋም ያሳውቃሉ፣

2. አመታዊ የስራ እቅድ አዘጋጅተው ለተቋሙ ያቀርባሉ፣
3. ከስነምግባር ግንባታ እና ሙስና መከላከል አንፃር ያሉትን ሁኔታዎች እያጠና ለተቋሙ ኃላፊ ያቀርባል፣
4. እንደ አስፈላጊነቱ የቀን፣ የሳምንት፣ የወር፣ የሩብ ዓመት፣ የ6 ወር እና የዓመትሪፖርት ለተቋሙ ለበላይ ኃላፊው ያቀርባል፣
5. ማንኛውንም ወቅታዊ ሪፖርቶች ለኮሚሽኑ ሲያሳውቅ በገልባጭ ለተቋሙ የበላይ ኃላፊም ያሳውቃል፣
6. በአስቸኳይ የሙስና መከላከል የሚሰሩትን ስራዎችን፣ የተፈጠሩ ሁኔታዎችን እና የሚፈቱበትን መንገድ ለተቋሙ የበላይ ኃላፊ ያቀርባል፣
7. የፀረ ሙስና ትግሉን ያስተባብራል፣ በሙስና መከላከል እና በስነምግባር ግንባታ የበላይ ኃላፊውን ያማክራል፣ የሰራተኛ ንቅናቄ እንዲፈጠር ያድርጋል::

## 10. የስነምግባር መከታተያ ክፍሎች የእቅድ፣ የሪፖርት፣ግብረ መልስ እና የስራ አፈፃፀም ስርዓተ

### 1. የእቅድ ዝግጅት እና አቀራረብ

1). ኮሚሽኑ አመታዊ የመነሻ እቅድ አዘጋጅቶ በየደረጃው ላሉ መከታታያ ክፍሎች ይልካል፣

2). የመከታተያ ክፍሉ የኮሚሽኑን መነሻ እና የመስሪያ ቤቱን ወይም የልማት ድርጅቱን ሁኔታ በዝርዝር ገምግሞ በዓመቱ ውስጥ ከተሰጡት ተግባር እና ኃላፊነቶች ውስጥ የሚያከናውናቸውን ተግባሮች እቅድ አዘጋጅቶ ለሚሰራበት መስሪያ ቤት ወይም የልማት ድርጅት እና ለኮሚሽኑ ከዝርዝር የድርጊት መርሃ ግብር ጋር ይልካል፣

3). በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (1) እና (2) መሰረት የተዘጋጀውን አመታዊ እቅድ ለመነሻ እንዲሆናቸው እና የራሳቸውን እቅድ አዘጋጅተው እንዲልኩለት ለቅርንጫፎች ይልካል፣

4). ከኮሚሽኑ እና ከመስሪያ ቤቱ ወይም ከልማት ድርጅቱ የሚሰጠውን ግብረ መልስ እና አስተያየት በማካተት የመጨረሻ እቅድ አዘጋጅቶ ወደ አፈፃፀም ይገባል፣



The Federal Ethics and Anti-Corruption Commission

5). ለእቅዱ ማስፈፀሚያ የሚያስፈልገውን ዓመታዊ የበጀት ፍላጎት በማዘጋጀት ለመስሪያ ቤቱ ወይም ለልማት ድርጅቱ አቅርቦ ያስመድባል።

2. የስራ አፈፃፀም ሪፖርት አቀራረብ

1) መከታተያ ክፍሉ የመስሪያ ቤቱን ወይም የልማት ድርጅቱን የቅርንጫፉን መከታተያ ክፍል የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርት በየወሩ፣ በየሩብ ዓመቱ፣ በግማሽ ዓመት፣ በ9ወር እና በአመት ይቀበላል፣አፈፃፀሙን ይገመግማል፣
2) መከታተያ ክፍሉ የዋናውን መስሪያ ቤት ወይም የልማት ድርጅት እና የቅርንጫፎችን የአፈጻፀም ሪፖርት በማከተት የተጠቃለለ የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ወቅቱን ጠብቆ ለመስሪያ ቤቱ ወይም ለልማት ድርጅቱ ለበላይ ኃላፊ እና ለኮሚሽኑ ያቀርባል።

3. የግብረ መልስ እና የድጋፍ አሰጣጥ ሥርዓት

1) የተቋሙ የበላይ ኃላፊ እና ኮሚሽኑ የስነምግባር መከታተያ ክፍሉ ኃላፊ የሚያቀርብለትን የአፈፃፀም ሪፖርት በመመልከት ተገቢ የሆነ ግብረ መልስ ይሰጣሉ፣
2) የመከታተያ ክፍሉ ኃላፊ ለቀረበው የቅርንጫፎች የአፈፃፀም ሪፖርት በየወሩ፣ በሩብ አመት እና በየግማሽ ዓመት ግብረ መልስ ይሰጣል፣
3) ኮሚሽኑ በዓመት ሁለት ጊዜ የአካል ድጋፍ፣ በየሩብ ዓመቱ ደግሞ የጹሁፍ ድጋፍ ያድረጋል፣
4) ኮሚሽኑ በዓመት ሁለት ጊዜ በማዕከል ደረጃ ከስነምግባር መከታተያ ክፍሎች ጋር የስራ አፈፃፀም ግምገማ እና የልምድ ልውውጥ ያደርጋል።

11. የስነምግባር መከታተያ ክፍል የስራ ቦታ

የስነምግባር መከታተያ ክፍሉ የስራ ቦታ የተመደበበት የመንግስት መ/ቤት ወይም የመንግስት የልማት ድርጅት የስራ ቦታ ይሆናል።

The Federal Ethics and Anti-Corruption Commission

## ክፍል ሶስት

## የስነምግባር መከታተያ ክፍል የሰው ኃብት አስተዳደር

### 12. ተፈላጊ የትምህርት ዝግጅት እና የስራ ልምድ

1. በማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም የመንግስት ልማት ድርጅት ውስጥ በስነምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊ ወይም ስራተኛ ሆኖ ለመመደብ በማንኛውም በሶሻል እና በተፈጥሮ ሳይንስ በመጀመሪያ ዲግሪ እና በላይ የተመረቀ መሆን ይኖርበታል፣
2. የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ዳይሬክተር ለመሆን በዶክትሬት ዲግሪ ተመርቆ 6 ዓመት፣ በማስትሬት ዲግሪ ተመርቆ 8 ዓመት እና በመጀመሪያ ዲግሪ ተመርቆ 10 ዓመት የስራ ልምድ ያለው መሆን አለበት፣
3. የሥነምግባር መከታተያ ቡድን መሪ ለመሆን በዶክትሬት ዲግሪ ተመርቆ 4 ዓመት፣ በማስትሬት ዲግሪ ተመርቆ 6 ዓመት እና በመጀመሪያ ዲግሪ ተመርቆ 8 ዓመት የስራ ልምድ ያለው መሆን አለበት፣
4. የሥነምግባር መከታተያ ባለሙያ IV ለመሆን በማስተሬ ዲግሪ ተመርቆ 4 ዓመት እና በመጀመሪያ ዲግሪ ተመርቆ 6 ዓመት የስራ ልምድ ያለው መሆን አለበት፣
5. የሥነምግባር መከታተያ ባለሙያ III ለመሆን በማስትሬት ዲግሪ ተመርቆ 2 ዓመት እና በመጀመሪያ ዲግሪ ተመርቆ 4 ዓመት የስራ ልምድ ያለው መሆን አለበት፣
6. የሥነምግባር መከታተያ ባለሙያ II ለመሆን በማስትሬት ዲግሪ ተመርቆ 0 ዓመት እና በመጀመሪያ ዲግሪ ተመርቆ 2 ዓመት የስራ ልምድ ያለው መሆን አለበት፣
7. የስራ ልምዱ የሚገኘው ከዲግሪ በኋላ በትምህርት መስኩ የተገኘ የሥራ ልምድ መሆን ይኖርበታል፣
8. የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊ እና ባለሙያ ሆኖ የሚመደብ ወይም የሚቀጠር ሰው ሲሰረባት በነበረው ተቋም ውስጥ በዲስፕሊን ያልተቀጣ፣ ከአደንዛዥ ዕፅ እና ከሌሎች ደባል ሱሶች ነፃ የሆነና ይህንኑ ሲሰራበት ከነበረው ተቋም ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል።

13. ምደባ

1. ኮሚሽኑ የስነምግባር መከታተያ ክፍል ዳይሬክተርን፣ የቡድን መሪን እና አንድ ብቻ ባለሙያ ባለባቸው ተቋማት ውስጥ ሁልጊዜም ሚራቱን ያሟሉትን በምደባ እንዲሟሉ ያደርጋል፡፡ ሌሎች ሰራተኞች ግን በሚሪት ማለትም በቅጥር፣ በደረጃ እደገት እና በዝውውር የሚሞሉ ይሆናል፣
2. በዚህ አንቀፅ በንኡስ አንቀፅ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽኑ ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ በየመንግስት መስሪያ ቤቱ እና ልማት ድርጅቱ አሁን በስራ ላይ ያሉትን ሁሉንም የስነምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊዎች እና ሰራተኞች የትምህርት ዝግጅታቸውን፣ የስራ ልምዳቸውን እና የስነምግባር ሁኔታቸውን በማየት የምደባ ስራ ያከናውናል፣
3. ኮሚሽኑ ምደባውን ከማካሄዱ በፊት በስራ ላይ ያሉት የስነምግባር መከታተያ ክፍሎቹ እና ሰራተኞቹ ከሚገኙበት ተቋም ጋር ምክክር ያደርጋል፣
4. ኮሚሽኑ በሚያካሄደው በምደባው ያልተካተቱ የመከታተያ ክፍል ኃለፊዎች እና ሰራተኞች ካሉ የሚገኙበት ተቋም በሚያሞሉት የስራ መደብ መመደብ ይኖርበታል፡፡

14. ቅጥር

1. ኮሚሽኑ በመንግስት መስሪያ ቤቶች ወይም በመንግስት ልማት ድርጅቶች ውስጥ የስነምግባር መከታተያ ክፍል ስራተኞች ክፍት የስራ መደብ ወይም አዲስ የተፈቀደ የስራ መደብ ሲኖር በቅጥር እንዲሟሉ ያደርጋል፣
2. የመንግስት መስሪያ ቤቶች ወይም የመንግስት ልማት ድርጅቶች ውስጥ የሚገኙ መከታተያ ክፍል ስራተኞች ክፍት የስራ መደብ ሲኖር ኮሚሽኑ በቅጥር እንዲያሟላ ለኮሚሽኑ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል፣
3. በመንግስት መስሪያ ቤቶች ወይም በመንግስት ልማት ድርጅቶች ውስጥ አዲስ ለሚቀጠሩ ለመከታተያ ክፍል ኃላፊዎች እና ሰራተኞች ስለስራቸው በቂ ግንዛቤ እንዲያገኙ ኮሚሽኑ የስራ ማስጀመሪያ ስልጠና ይሰጣል ወይም እንዲሰጡ ሊያደርግ ይችላል፡፡

15. **የደረጃ እድገት**

1. ኮሚሽኑ በመንግሥት መ/ቤቶች ወይም በመንግስት ልማት ድርጅቶች የውስጥ የመከታተያ ክፍል ኃላፊዎች ወይም ሰራተኞቸ ክፍት መደብ ሲኖር በደረጃ ዕድገት እንዲሟሉ ያደርጋል፣
2. የደረጃ እድገት የሚወጣው አሁን በስራ ላይ ላሉት የስነምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊዎች ወይም ሠራተኞች ወይም ለሌሎች የመስሪያ ቤቱ ወይም የልማት ድርጅቱ ሠራተኞች ይሆናል፡፡
3. በስራ ላይ ያሉት የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊ እና ሰራተኞች በሚሰሩበት የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም በመንግስት የልማት ድርጅቱ ውስጥ በሚወጣ የደረጃ እደገት እንደ ማንኛውም እንደ ተቋሙ ተወዳዳሪ ሰራተኛ መወዳደር ይችላሉ፣
4. ኮሚሽኑ ክፍት የሆኑ የሥራ መደቦችን ካሰባሰበ በኋላ የደረጃ ዕድገት ማስታወቂያ አውጥቶ በውስጥ ሰሌዳ፣ ክፍት መደቡ በአለበት ተቋም ላይ እንዲለጠፍ እና በኮሚሽኑ ድረ-ገጽ እንዲወጣ ያደርጋል፣
5. ኮሚሽኑ ለደረጃ ዕድገት ያመለከቱ ተወዳዳሪዎችን በደረጃ ዕድገት አሰጣጥ መመሪያዎች መሠረት አወዳድሮ አሸናፊውን በመለየት ክፍት የሥራ መደቡ ላለበት የመንግሥት መስሪያ ቤቱ ወይም የመንግስት የልማት ድርጅቱ ደርጅቱ ይልካል፡፡

16. **ዝውውር**

1. ኮሚሽኑ በመንግስት መስሪያ ቤቶች ወይም በመንግስት የልማት ድርጅቶች የመከታታያ ክፍል ኃላፊዎችን እና ሠራተኞችን በተመሳሳይ የስራ ደረጃ አዛውሮ ማስራት ይችላል፣
2. በአንድ የመንግሥት መ/ቤት ወይም የመንግስት የልማት ድርጅት የመከታተያ ክፍል ውስጥ ክፍት የሆነ የሥራ መደብ ሲኖር ተዘዋውረው ለመስራት የሚፈልጉ የስነምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊዎች ወይም ሰራተኞች ካሉ ኮሚሽኑ በሚያወጣው የዝውውር ማስታወቂያ መሰረት ዝውውር ሊፈፀም ይችላል፣
3. ኮሚሽኑ እንደ አስፈላጊነቱ አንድን የመከታተያ ክፍል ሠራተኛ እኩል በሆነ የሥራ ደረጃ ከአንድ የመንግሥት መ/ቤት ወደ ሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት አዘዋውሮ ሊያሰራ ይችላል፣

4. ከአንድ የመንግስት የልማት ድርጅት ወደ ሌላ የመንግስት የልማት ድርጅት የተቋም መሪዎች ፈቃደኝነትን በአረጋገጠ ሁኔታ አዛውሮ ማሰራት ይቻላል፣

## 17. የሥራ አፈፃፀም ምዘና ስርዓት

1. የመከታተያ ክፍል የሥራ አፈጻጸም ዕቅድ የሚዘጋጀው ከተቋሙ ስትራቴጅያዊ ግቦች ጋር በተመጋገበ ወይም የወሳኝ የሥራ ሂደቶችን ግቦች ባገናዘበ አግባብ ይሆናል፣
2. ሠራተኞች ስለሚጠበቅባቸው ተግባራት፣ ኃላፊነቶችና ውጤቶች በግልጽ እንዲረዱና የአፈጻጸም ግብረ መልስም ቀጣይነት ባለው መልኩ እንዲያገኙ መደረግ አለበት፣
3. ኮሚሽኑ ለመከታተያ ክፍል ኃላፊው እና ለሚሰራበት ተቋም በቅድሚያ የዕቅድ ስምምነት በጽሁፍ እንዲደርሰው ያደርጋል፣
4. የመከታተያ ክፍል ኃላፊው በቅድሚያ የዕቅድ ስምምነት ለመከታተያ ክፍል ሠራተኞች በጽሁፍ እንዲደርሳቸው ያደርጋል፣
5. የሠራተኞች አፈጻጸም ምዘና አስቀድሞ ስምምነት በተደረሰባቸው ግብ ተኮር ተግባራት፣መለኪያዎችና የአፈጻጸም ደረጃዎች መሰረት ዕቅድንና አፈጻጸምን በማነጻጸር የሚለካ ይሆናል፣ የሚለካውም በሠራተኛው ክንውን ወይም ውጤት መሠረት ይሆናል፣
6. የመከታተያ ክፍል ኃላፊዎች በሥራቸው የሚገኙትን ሠራተኞች የሥራ አፈጻጸም ምዘና ወቅቱ ተጠብቆ እንዲሞላ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፣
7. የመከታተያ ክፍሉ ኃላፊ በስሩ ያሉትን ሰራተኞች እና የቅርንጫፍ መከታተያ ክፍል ኃላፊውን የስራ አፈጻጸም ይመዝናል፣ ውጤቱንም በየግማሽ ዓመቱ ለኮሚሽኑ ይልካል:: ምዘናው ከ80% በመከታተያ ክፍሉ ኃላፊ ሲሆን ቀሪው ከ20% ደግሞ በቅርንጫፉ ኃላፊ የሚሞላ ይሆናል፣
8. የቅርንጫፍ መከታተያ ክፍል ኃላፊው በስሩ ያሉትን ሰራተኞች የስራ አፈፃጸም ይመዝናል፣
9. ኮሚሽኑ እና የተቋሙ የበላይ ኃላፊ የመከታተያ ክፍሉን ኃላፊ የስራ አፈፃፀም ይመዝናሉ፣ ውጤት ይሞላሉ፣ ውጤቱን ለተመዛኙ ያሳውቃሉ፣
10. በምዘናው የሚሰጠው ውጤት ከ80% በኮሚሽኑ ሲሆን ከ20% ደግሞ በተቋሙ የበላይ ኃላፊ ይሆናል:: አሞላሉ በተቋሙ የበላይ ኃላፊ ከሚሞላው 20% ውስጥ

10% የስራ አፈፃጸም ሲሆን 10% ደግሞ የባህሪ ምዘና ሆኖ ኮሚሽኑ በሚልከው የውጤት መሙያ ቅፅ መሰረት ሞልቶ ለኮሚሽኑ ይልካል፡፡ ኮሚሽኑ ደግሞ ከ80% የስራ አፈፃፀም ሞልቶ የተጠቃለለውን ውጤት የስነምግባር መከታተያ ክፍሉ ለአለበት ተቋም ይልካል፣

11. የአፈጻጸም ምዘና እና ምዘናውን መሰረት በማድረግ የሚሰጡ ውሳኔዎች በጽሁፍ የተደራጁ መሆን አለባቸው፡፡

## 18. የፈቃድ አሰጣጥ

1. ለመከታታያ ክፍል ሠራተኞች የዓመት ዕረፍት ፈቃድ እና ሌሎች ልዩ ልዩ ፈቃዶች በሚያቀርቡት ዓመታዊ እቅድ መሰረት በመከታታያ ክፍሉ ኃላፊ ይሰጣቸዋል፣
2. የመንግሥት መ/ቤቶች ወይም የመንግስት የልማት ድርጅቶች በስራቸው ለአሉት የመከታተያ ክፍል ኃላፊዎች በሚያቀርቡት የዓመት ዕረፍት ፈቃድ እቅድ እና ሌሎች ልዩ ልዩ ፍቃዶች ከኮሚሽኑ ጋር በመነጋገር ይሰጣሉ፣
3. የዓመት ዕረፍት ፈቃድ አስገዳጅ ሁኔታ ከአለጋጠመ በስተቀር ወደ ሚቀጥለው በጀት ዓመት አይተላለፍም፡፡ ሆኖም ግን አስገዳጅ ሁኔታ ሲያጋጥም ግን የዓመት ፍቃድ ወደ ሚቀጥለው የበጀት ዓመት ይተላለፋል፡፡

## 19. የሥራ መልቀቂያ

1. በመንግስት መስሪያ ቤቶች ወይም በመንግስት ልማት ድርጅቶች ለሚሰሩ የመከታታያ ክፍል ኃላፊ መልቀቂያ የሚሰጠው ኮሚሽኑ ነው፣
2. ለመከታተያ ክፍል ሠራተኞች የሥራ መልቀቂያ የሚሰጠው የመከታተያ ክፍል ኃላፊው ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን የመከታተያ ክፍል ኃላፊው ሰራተኛው የለቀቀ መሆኑን ለኮሚሽኑ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

## 20. የሥራ ልምድና መረጃ አያያዝ

1. የመከታተያ ክፍል ኃላፊዎች እና ሠራተኞች የሥራ ልምድ፣ ዋስትና እና ሌሎች ልዩ ልዩ አገልግሎቶች በሚሰሩበት ተቋም እንዲሰጥ ያደረጋል፡፡
2. የተቋሙ የስነምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊና ሠራተኞችን ፕሮፋየል ኮሚሽኑ በሚልከው ቅፅ መሰረት አዘጋጅቶ ይይዛል፣ሲጠየቅም ለኮሚሽኑ ይልካል፣

## 21. ስለተከለከለ ድርጊት

በስራ ላይ ያለ የኮሚሽኑ ሠራተኛ ለስነምግባር መከታተያ ክፍሎች በምደባም ይሁን በዝውውር በሌሎች ተቋማት ውስጥ በስነምግባር መከታተያ ሠራተኝነት የስራ ስምሪት ሊሰጠው አይችልም፡፡

## ክፍል አራት

## የስነምግባር መከታታያ ክፍል የስነስርዓትና የዲስፐሊን እርምጃ አወሳሰድ

## 22. የስነስርዓት እና የዲሲፐሊን ጉድለት ክስ አጀማመር

1. የስነስርዓት እና የዲስፐሊን ጉድለት እርምጃ አወሳሰድ የሚጀመረው በመከታተያ ክፍሉ ላይ በሚቀርቡ ጥቆማዎች ወይም ተገልጋዮች በሚያቅርቡት አቤቱታ ወይም ተግባሩን ሲያከናውን በፈፃማቸው ግድፈቶች ወይም በተደረገ ክትትል ላይ ተመስርቶ ይሆናል፣

2. የተቋሙ የበላይ ኃላፊ በስነምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊ ወይም ሰራተኛ ላይ የዲሲፒሊን ግድፈት ተፈፅሟል የሚል ጥቆማ ሲደርሰው ለኮሚሽኑ ይልካል፣
3. ኮሚሽኑ በመከታተያ ክፍል ኃላፊ ወይም ሰራተኛ ላይ የዲሲፐሊን ግድፈት ከላይ በንኡስ አንቀፅ 1 እና 2 መሰረት ሲደረሰው ተቀብሎ ያጣራል፡፡

## 23. ምርመራ ስለማጣራት እና  ክስ ስለመመስረት

1. የኮሚሽኑ የሰው ሃብት አስተዳደር ጥቆማ በቀረበበት የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊ ወይም ሰራተኛ ክስ መስርቶ ለኮሚሽኑ ዲሲፐሊን ያቀርባል፣
2. የዲሲፐሊን ኮሚቴው የቀረበለትን ክስ መሰረት በማድረግ ማስረጃ ያሰባስባል ምርመራ ያካሂዳል፣

3. የተቋቋመው አካል ወይም ኮሚቴ የደረሰውን ጥቆማ ወይም በክትትል የተገኘውን መሰረት አድርጎ ማስረጃ ይሰበስባል፣ ያጣራል፣ ክስ ለመመስረት በቂ መሆኑን ያረጋግጣል፣
4. የዲሲፒሊን ኮሚቴው ክስ ከመመስረቱ በፊት ክስ ለመመስረት የሚያስችል ማስረጃ የለም ወይም የቀረበው ጥቆማ ተገቢ አይደለም ብሎ ከመነ ይኸንኑ ለኮሚሽነሩ

ያቀርባል፡፡ ነገር ግን በመከታተያ ክፍሉ ላይ የቀረበው ጥቆማ ተገቢ እና ክስ ለመመስረት በቂ ማስረጃ አለ ብሎ ካመነ ክርክሩ እንዲሰማ ያደረጋል፣

5. ከዚህ በላይ በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ 4 ላይ በቂ ማስረጃ የለም ብሎ ያቀረበውን ኮሚሽነሩ ክስ ለመመስረት በቂ ማስረጃ አለ ብሎ ከወሰነ አስፈላጊውን ማስረጃ እንደገና አሰባስቦ ክርክሩ እንዲቀጥል ያደርጋል፡፡

## 24. ክርክርን ስለማስማት

1. ክስ የተመሰረተበት የስነምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊ ወይም ሰራተኛ በኮሚሽኑ ሰው ሃብት አስተዳደር አማካኝነት ክሱ እና መጥሪያ ይለክለታል፡፡ በመጥሪያው ላይ የተከሰሰበት ጉዳይ፣ ለመቼ እንደሚቀብ፣ የት ቦታ መቅረብ እንዳለበት እና የክሱን መልስ በ3 ኮፒ በፁሁፍ ይዞ እንዲቀርብ መገለጽ አለበት፡፡ በክስ ላይ የማስረጃ አይነት እና ዝርዝር አብሮ መላክ ይኖርበታል፣

2. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት መጥሪያ እና ክስ ደርሶት በእለቱ መልስ ይዞ በአካል ወይም በህጋዊ ወኪሉ አማካኝነት ከአልቀረበ ክሱ በሌለበት መታየት እንደሚጀምር በመጥሪያው ላይ መገለፅ ይኖርበታል፣
3. ክስ የቀረበበት የመከታታያ ክፍል ኃላፊ ወይም ሰራተኛ ክስ እንደሚታይ በመጥሪያው ላይ በተገለፀው መሰረት ተከሳሹ ወይም ህጋዊ ወኪሉ እና ከሳሽ መቅረባቸው ተረጋግጦ ክሱ ይነበብለታል፡፡ ተካሳሽ ክሱን ሰምቶ መልስ ካለው በፁሁፍ በሶስት ኮፒ እንዲያቀረብ መደረግ ይኖረበታል፡፡ በመልሱ ላይ የመጀመሪያ ደረጃ መቀወሚያ ካለው ይህንኑ በመልሱ ላይ ማቅረብ አለበት፡፡ ከአላቀረበ ግን የመጀመሪያ ደረጃ መቀዋሚያ እንደሌለው ተቆጥሮ የፍሬ ነገር ክርክሩ ይገባል፣
4. ክርከሩን የሚሰማው አካል ከሳሽ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ካለው በመጀመሪያ ደረጃ መቀወሚያው ላይ ብይን መስጠት አለበት፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ መቀወሚያውን ክርክሩን የሚሰማው አካል ከተቀበለው አስፈላጊውን ትዕዛዝ ይሰጣል፣
5. የመጀመሪያ ደረጃው መቀዋሚያ ተቀባይነት ከሌለው ማስረጃ እንዲሰማ ያዛል፣
6. በክርክሩ ላይ የሰው ማስረጃ ከአለ ቀርበው እንዲሰሙ መጥሪያ ይለካል፡፡ ተከሳሽም ምስክሮች በሚሰሙበት እና ማስረጃ በሚሰማበት ቀን ቀርቦ የቀረበበትን የሰው ምስክር የማደማጥ፣ መስቀለኛ ጥያቄ የማቅረብ እና የመመርመር መብት አለው፣



The Federal Ethics and Anti-Corruption Commission

7. ክሱን የሚሰማው አካል ምስክሮቹ ወይም የቀረቡት ማስረጃዎች እንደ ክሱ አቀራረብ አስረድተዋል ብሎ ከአመነ ጥፋተኛ ነህ ብሎ ተከሳሽ ክሱን እንዲከላከል ወይም የመከላከያ ምስክር ከአለው እንዲያቀርብ እድል ይሰጠዋል፣
8. በመጨረሻ ክክርክሩን የሰማው አካል ለተከሳሹ ውሳኔው መቼ፣ ውሳኔው በየት በኩል እንደሚደረሰው እና በውሳኔው ቅር ከተሰኘ ይግባኝ የማለት መብት እንደለው ገልፆ ተከሳሹን ያሰነብተዋል፡፡

## 25. ውሳኔ አሰጣጥ

1. ክሱን እና ማስረጃውን የመረመረው አካል ተካሳሹ የተከሰሰበትን ድርጊት፣ የተከሰሰበትን ድንጋጌ እና ማስረጃውን በመመርመር ውሳኔውን በጥንቃቄ ይወስናል፡፡
2. ክርክሩን የሠማው በውሳኔው ላይ የተከሰሰበትን ድርጊት፣ የቀረበውን መልስ፣ የተሰሙትን የምስክሮች ቃል፣ የጣሰውን ድንጋጌ እና የሚያስከተለውን ቅጣት መግለፅ አለበት፡፡ ተካሳሹ የቀረበበት ማሰረጃ የማያስቀጣው እና ጥፋት የለውም ብሎ ከአመነ ይህንኑ በግልፅ ማስቀመጥ አለበት፣
3. በመጨረሻም የውሳኔ ሃሳቡን ለኮሚሽኑ ኮሚሽነር ማቅረብ አለበት፡፡

## 26. የውሳኔው አፈጻጸም

1. የቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ኮሚሽነሩ ከአፀደቀው ይኸው እንደሚፈፀም ለሚመለከተው አካል መላክ አለበት፣
2. ኮሚሽነሩ የሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፣
3. ተከሳሽ በውሳኔው ላይ ቅር ከተሰኘ ይግባኝ የመስማት ስልጣን ለአለው አካል የማቅረብ መብት አለው፣

## 27. በዲሲፕሊን የሚያስቀጡ ጥፋቶች

ቀላል እና ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋቶች የሚባሉት እና የሚያሥከትሉት ቅጣቶች በስራ ላይ በአለው በኮሚሽኑ የአስተዳደር ደንብ መሰረት ይሆናል፡፡

28. ስለይርጋ

1. ቀላል የዲሲፕሊን ቅጣት የሚያስከትል ጥፋት የፈፀመ የኮሚሽኑ ሠራተኛ የምርመራውን ጊዜ ሳይጨምር የፈፀመው ጥፋት ከታወቀበት ቀን ጀምሮ እስከ ስድስት ወር እርምጃ ካልተወሰደበት በዲሲፕሊን ተጠያቂ አይሆንም፣

2. ከባድ የዲሲፕሊን ቅጣት የሚያስከትል ጥፋት የፈፀመ የኮሚሽኑ ሠራተኛ የፈጸመው ጥፋት ከታወቀበት ቀን ጀምሮ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ በጥፋቱ ካልተከሰሰ በዲሲፕሊን ተጠያቂ አይሆንም፣

3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 1 ወይም 2 በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ መወሰድ የሚገባውን የዲሲፕሊን እርምጃ ሳይወስድ የቀረው ኃላፊ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

29. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ለዚህ መመሪያ ተግባራዊነት የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

30. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ ህጎች እና ልማዳዊ አሰራሮች በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

31. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከመጋቢት 21 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ፤ መጋቢት 21 ቀን 2013 ዓ.ም

ፀጋ አራጌ

የፌዴራል የስነምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር